ወርኃዊ ጥንቅር ቁጥር 3
ግንቦት 2017 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

## እንደራሴ

እንደራሴ በብርጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy


+251 911 86 12 34

+251 115 57 74 96

research@bridge-et.org

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


በግንቦት የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ሥብሰባዎች ..................................1

የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ..................................................2

የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ..................................................... 5

የፓርላማ ዲፕሎማሲ ..................................................................... 11

እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው ............................................................13

ኢትዮጵያ ምን ተስማማች? ..........................................................14

የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታዎች ..........................................................15

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኃ ግንቦት የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን ከውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግጋት ማውጣት፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ፣ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ እና የፌደራል ተቋማትን መጎብኘት የሚጠቀሱት የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖቹ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም፣ ምክር ቤቱ የራሱን የዘጠኘ ወራት ሥራ አፈፃፀም ጨምሮ፣ ለእንደራሴዎቹም የዐቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እንዲሰጥ ሲያደርግ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩንም ወደ አዳራሹ ጠርቶ በተለያዩ ውጭ ጉዳይ ተኮር ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ እንዲሰጠው አድርጓል። ይኽች የብሪጅ ሣሥተኛ ዕትምም፣ እኒህን የምክር ቤቱን የግንቦት ክራሞት ጨምሮ፣ በወሩ ከጸደቁት ሕግጋት መካከል በመረጥነው አንድ ሕግ ላይ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለዴሞክራሲያዊ ፓርላሜንታዊ ስርዓት ግንባታ ስለሚኖረው ሚና አጭር ተቋማዊ ዳሰሳዊ ምልክታችንን አካታ ቀርባለች።

# በግንቦት የተካሄዱ የምክር ቤቱ መደበኛ ሥብሰባዎች

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት የስራ ዘመን

**ግንቦት 5**

29ኛ መደበኛ ስብሰባ

- በኢትዮጵያ እና በጣሊያን መንግስት መካከል ለአካባቢያዊና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የበጀት ድጋፍ ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ማጽደቅ፤
- በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለመማር ማስተማር ማጎልበቻ የትምህርት ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ማጽደቅ፤
- በአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ ስምምነት አዋጅ ስምምነትን ማጽደቅ፤
- በኢትዮጵያ እና በኦስትሪያ ፌዴራል መንግስት መካከል የተፈረመውን የአየር ትራንስፖርት ስምምነት አዋጅ ማጽደቅ፡፡

**ግንቦት 12**

30ኛ መደበኛ ስብሰባ

- የከተማ መሬት ይዞታ እና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ አዋጅን ማጽደቅ፤
- የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሚሆኑበትን አግባብ ለመደንገግ የወጣ ረቂቅ አዋጅን ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መምራት፡፡

**ግንቦት 14**

31ኛ መደበኛ ስብሰባ

- የውሃ አካል ዳርቻ አወሳሰን፣ ልማት እና እንክብካቤ አዋጅን ማጽደቅ፡፡

**ግንቦት 19**

32ኛ መደበኛ ስብሰባ

- የተመራው የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ አዋጅ መመርመር እና ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መላክ፤
- የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን መመርመር እና ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መላክ፤
- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር ዶ.ር. ኢ/ር ሀብታሙ ኢተፋን ማብራሪያ ማዳመጥ፤

**ግንቦት 26**

33ኛ መደበኛ ስብሰባ

- በኢትዮጵያ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል ለተቀናጀ የውጤታማ ግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ለወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ማጽደቅ፤
- በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለሴቶች እና ልጃ-ገረዶች ጤና የተቀናጀ፣ ጠንካራ እና በፈጠራ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የቀረበውን የብድር ስምምነት ማጽደቅ፤
- የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅን ማጽደቅ፤

**ግንቦት 28**

34ኛ መደበኛ ስብሰባ

- የኢትዮድያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አዋጅን ማጽደቅ፤
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቲዎስን ማብራሪያ ማዳመጥ፤

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት የስራ ዘመን

# የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የተወካዮች ምክር ቤት፣ በጠቀስነው ግንቦት ወር ውስጥ አራት ሕግጋትን ሲያጸድቅ፣ ሦሥት ረቂቅ አዋጆችን ደግሞ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ለዝርዝር ዕይታ ልኳል፤ ከዚኽ በተጨማሪም፣ አንድ የአስረጂ መድረክ አካሂዷል።

## የጸደቁ ሕግጋት

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሳለፍነው ግንቦት 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ካጸደቃቸው ሕግጋት መካከል አንዱ፣ የመሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማዘመን ያስችላል የተባለውን፣ 'የከተማ መሬት ይዞታ እና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ' ረቂቅ አዋጅን ነበር። 30ኛውን መደበኛ ስብሰባውን ሲያካሂድ ረቂቅ አዋጁን ለተመለከተው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ አቅርበዋል፡፡ ምክትል ሰብሳቢው፣ በአገር ደረጃ ወጥነት ባለው መልኩ በኹሉም ከተሞች የሚገኙትን የመሬት ይዞታዎች መረጃ ለማደራጀት እና ለመተግበር ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት አዋጁ አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ተናግረዋል። አክለውም፣ ረቂቅ አዋጁ ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራን፣ ብልሹ አሰራርን እና ኢ-ፍትሓዊነትን በማስቀረት የዜጎችን የመሬት ይዞታ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ከፍ ያለ አበርክቶ ይኖረዋል ሲሉ ለእንደራሴዎቹ አብራርተዋል።

የዜጎችን የመሬት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ነው የተባለውን ይኽንኑ አዋጅ አስመልክቶም፣ በከተማ አሥተዳደሮች እና የክልል ከተሞች ያላቸውን ልዩነት እና አንድነት በግልፅ በረቂቅ አዋጁ ማመላከት እንደሚገባ እንደራሴዎቹ አሳስበዋል፡፡ ምክር ቤቱም የቀረበለትን ይኽንኑ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1381/2017 አድርጎ በኹለት ተቃውሞ እና በሦሥት ድምጸ-ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በወርኃ ግንቦት ያጸደቀው ሌላይኛው አዋጅ፣ የውኃ አካል ዳርቻ አወሳሰን፣ ልማት እና እንክብካቤ ረቂቅ አዋጅን ነበር። በአዋጁ ዙሪያ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ፣ የውኃ አካል ዳርቻን በዘላቂነት ለማልማት እና ለመንከባከብ የውኃ ሥነ-ምኅዳር አግልግሎትን በማሻሻል ለአካባቢው ማኅበረሰብ ተጨማሪ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ ዘርዝረ አድርገው አብራርተዋል። የአዋጁን ዋንኛ ይዘቶች ያነሱት ሰብሳቢው፣ የውኃ አካል ወንዝ ዳርቻን፣ ሐይቅ፣ ግድብ፣ ውኃ አዘል መሬት፣ ምንጭ እና የከርሰ ምድር ውኃ አያያዝ እና አጠቃቀምን አዋጁ እንደሚደነግግ ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋል። ከዚኽ ባለፈም፣ በተከለለ የውኃ አካል ዳርቻ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ነባር ልማት ባለበት ኹኔታ ሊቀጥል የሚችለው በውኃ አካሉ እና ብዝሓ ሕይወቱ ላይ ጉዳት እና ብክለት የማያስከትል መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ መሆኑን ምክትል ሰብሳቢው አሳስበዋል። እንደራሴዎቹም፣ ረቂቅ አዋጁን፣ አዋጅ ቁጥር 1382/2017 ብለው በሙሉ ድምጽ እንዲጸደቅ ፈቃዳቸው ሆኗል።

33ኛ መደበኛ ስብሰባውን ግንቦት 26 ቀን 2017 ዓ.ም. ያካሄደው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በሦሥተኛነት ያጸደቀው ረቂቅ አዋጅ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ተብሎ የተጠራውን ረቂቅ አዋጅ ነበር። ይኽንኑ አዋጅ አስመልክቶም፣ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ ሲሆኑ፣ አዋጁ በአካባቢ እና በሰዎች ደኅንነት እና ጤና ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ያስችላል ሲሉ ለእንደራሴዎቹ ጠቅሰውላቸዋል። በአዋጁ የተቀመጠው ቅጣት አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ስስ

የፕላስቲክ ምርቶችን ታሳቢ ያደረገ ነው ሲሉ የተሰሙት አወቀ፣ ክልሎች እና ኹለቱ የከተማ አሥተዳደሮች የከተሞቻቸውን ነባራዊ ኹኔታ ታሳቢ በማድረግ የውስጥ ደንብና መመሪያ አውጥተው መተግበር እንደሚችሉ ጠቁመዋል። ረቂቅ አዋጁ የአካባቢ ሥነ-ምኅዳርን ለመጠበቅ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን የጠቀሱት እንደራሴዎቹ በበኩላቸው፣ ከአዋጁ ትግበራ ጋር በተያያዘ ማኅበረሰቡ በግንዛቤ ዕጥረት ለቅጣት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ሰፊ የግንዛቤ ሥራ መሰራት እንዳለበት ለቋሚ ኮሚቴው ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ረቂቅ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1383/2017 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል፤ (ስለዚኹ አዋጅ የብሪጅን ዳሰሳዊ ምልከታ ገጽ 15 ላይ ይመልከቱ)።

የኢትዮጵያ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ግንቦት 28 በነበረው 34ኛ መደበኛ ስብሰባው ያጸደቀው አራተኛው አዋጅ፣ የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ረቂቅ አዋጅን ነበር። ከኹለት ወራት በፊት ለምክር ቤቱ የቀረበውን ይኽንን አዋጅ አስመልክቶ የተናገሩት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈቲህ ማህዲ፣ አዋጁ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር መንግሥት መር፣ በአገር በቀል አቅም የተገነባ ብቻም ሳይሆን፣ ከጥገኝነት እና ከጠባቂነት አስተሳሰብ የሚያላቅቅ ጠንካራ ሐሳብን የያዘ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ አብራርተዋል፡፡ እንደ ምክትል ሰብሳቢዋ ገለጣም፣ ረቂቅ አዋጁ ሲዘጋጅ የፌደራል ሥርዓትን ከሚከተሉ ዘጠኝ አገራት ተሞክሮ የተወሰደበት በዓይነቱ ልዩ የሆነ አዋጅ በመሆኑ እንደራሴዎቹ እንዲያጸድቁት ጠይቀዋል፡፡ ወደፊት ለሚቋቋመው የአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ፣ ከመንግሥት እና ከግል ተቋማት ሠራተኞች ደመወዝ መዋጮ እንዲሰበሰብ የሚያስገድደው የአዋጁ ድንጋጌ ግን መሰረዙ ታውቋል። ድንጋጌው ከረቂቅ አዋጁ እንዲወጣ የተደረገው፣ በሠራተኞች ላይ ተደራራቢ ጫና እንዳያስከትል ታስቦ ነውም ተብሏል። ለፈንዱ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ከሚጠበቁት ውስጥ፣ የቴሌኮሚዩኒኬሽን ድምጽ እና ዳታ አገልግሎት፣ የዲጂታል ባንኪንግ፣ የበረራ ትኬት ሽያጭ፣ የፓስፖርት እና ቪዛ አገልግሎት ክፍያ፣ የንግድ ፈቃድ በሚወጣበት እና በሚታደስበት ጊዜ በቁርጥ የሚታሰብ ክፍያ ተጠቃሾቹ ምንጮች ናቸው። ባንኮች፣ አነስተኛ እና ጥቃቅን የፋይናንስ ድርጅቶች ከሚሰጡት የብድር መጠን ላይ የሚታሰብ ገንዘብም ሌላው የፈንዱ የገቢ ምንጭ ነው ተብሏል። በአዋጁ መሰረት የሚጠበቅበትን ገቢ ሰብስቦ ለአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ የባንክ ሒሳብ ያላስተላለፈ ድርጅት ወይም ተቋም፣ ሊያስገባው ይገባ ከነበረ ገንዘብ በተጨማሪ ዐሥር ከመቶ የባንክ ወለድ ቅጣት እንዲከፍል ያስገድዳል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ፣ የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1386/2017 በሚል ስያሜ በሙሉ ድምፅ አጽድቆታል፡፡

## ረቂቅ ሕጎች

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት 12 በነበረው ስብሰባው፣ የሚመለከታቸው ኹለቱ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የመራው ረቂቅ አዋጅ፣ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሚሆኑበትን አግባብ ለመደንገግ የወጣውን ረቂቅ አዋጅ ነበር። የረቂቁን አስፈላጊነት አንስተው ያብራሩት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ነበሩ። እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያም፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያ የተስተዋለው ከፍተኛ የከተሞች እና የውጭ መዋዕለ-ንዋይ ፍሰት መበርከት፣ የሰዎች ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት፣ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት እና መሰል ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጦች፣ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎት እንዲከሰት አድርጓል። ይኽን ከፍተኛ የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎት እና አቅርቦት ክፍተት ከመሙላት እና ተጨማሪ የፖሊሲ ግቦችን ከማሳካት አንጻር፣ መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን ሲያጤን ሰንብቷል ያሉት ተስፋዬ፣ ከእነዚኽ ውስጥ አንዱ የውጭ ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም የመኖሪያ ቤት ባለቤት መሆን የሚችሉበት የፖሊሲ አሠራር መሆኑን በቀኑ ለታደሙት እንደራሴዎች ነግረዋቸዋል።

የተወሰኑ እንደራሴዎችም፣ ረቂቁ ኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ክምችት እንዲኖራት ከመርዳቱ ባለፈ፣ መዋዕለ-ንዋይን ለመሳብ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ሲናገሩ ተደምጠዋል። ሌሎች እንደራሴዎች በበኩላቸው፣ ረቂቅ አዋጁ የዜጎችን የቤት ባለቤትነት የሚጋፋ፣ የቤት ዋጋ እንዲያሻቅብ የሚያደርግ እና ብሔራዊ የፀጥታ ስጋት ሊያስከትል ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ሲናገሩ ተስተውለዋል። አዋጁ ጊዜውን የጠበቀ አይደለም ሲሉ የተደመጡት እኚኹ እንደራሴዎች፣ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚጣረስ አዋጅ እያወጣን እንዳይሆን ሲሉም ስጋታቸውን ለምክር ቤቱ አጋርተዋል።

የተወሰኑ አገራት ዜጎች የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ እንዳይሆኑ የሚከለክል መመሪያ ወደፊት ሊወጣ እንደሚችል የሚደነግገው ይኸው አዋጅ፣ ለውጭ ዜጎች የተገደቡ ልዩ ቦታዎች እና የድንበር አካባቢዎችም እንዲኹ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ ሲል ያትታል። ረቂቅ አዋጁ በዋናነት ለከተማ፣ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤ በተባባሪነት ደግሞ ለሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሦሥት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ተመርቷል፡፡

በዚኹ ወርኃ ግንቦት፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ባካሄደው 32ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በአንድ ቀን ሌሎች ኹለት ረቂቅ አዋጆችንም ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል፡ ፡ ግንቦት 19 በዋለው በዚኹ መደበኛ ስብሰባ፣ እንደራሴዎቹ በቀዳሚነት የተመለከቱት፣ የሥርዓተ-ምኅዳር አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ አዋጅን ሲሆን፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ አጠር ያለ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡ የአዋጁን መዘጋጀት አስፈላጊነት በዚኹ ማብራሪያቸው ላይ ያነሱት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ተለያይነት ባላቸው ሥርዓተ-ምኅዳሮች የበለፀገች እና እነዚኽ ሥርዓተ ምኅዳሮች በአገራዊ የልማት ጥረቶች ላይ ያላቸውን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ አስተዋፅኦ ማሳደግ ማስፈለጉ መሆኑን ጠቅሰዋል። ሚኒስትር ዶ.ር. ተስፋዬ አክለውም፣ እነዚኽ ሥርዓተ-ምኅዳሮች ዘላቂ ባልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምክንያት በከፍተኛ ጫና ውስጥ በመሆናቸው፣ እነርሱን በዘላቂነት ለማሥተዳደር የሚያስችል



የሥርዓተ-ምኅዳር አገልግሎት ክፍያ የሕግ ማዕቀፍ ነባራዊ አስፈላጊነት አለው ሲሉም ተደምጠዋል። እንደራሴዎቹም፣ ይኽንኑ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 18/2017 ለዝርዝር ዕይታ በዋናነት ለውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤ በተባባሪነት ደግሞ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይመለከቱት ዘንድ መርተውላቸዋል።

በተጠቀሰው ዕለት እንደራሴዎቹ በኹለተኝነት የተመለከቱት ረቂቅ አዋጅ ደግሞ፣ የባለብዙ ተዋንያን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና አሥተዳደር የተሰኘው ረቂቅ ነበር። በተመሳሳይ በዚኹ ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ የተናገሩት የመንግሥት ተጠሪው ተስፋዬ በልጅጌ፣ በኢትዮጵያ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ አሥተዳደር እና ልማት እንዲኹም በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ያለውን የጥራት፣ አቅም እና የአፈጻጸም ውስንነትን ለመቅረፍ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት የሚያግዝ አዋጅ ነው ሲሉ አጠር ባለው ማብራሪያቸው አንስተዋል። ከዚኹ ባለፈም፣ በመንግሥት ብቻ ሲሰጥ የቆየውን የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አንስቶ የግል ዘርፉን እና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን በማቀናጀት ደረጃውን የጠበቀ የግብርና ኤክስቴንሽን የአገልግሎት እና የአሥተዳደር የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ ስለመሆኑ ማስረዳታቸውን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ዘገባ ያመለክታል። በመጨረሻም ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 19/2017 ለዝርዝር ዕይታ ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምጽ ይመራ ዘንድ እንደራሴዎቹ ፈቃዳቸው ሆኗል።

## አስረጂ መድረክ

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጠቀስነው ወርኃ ግንቦት አንድ የአስረጂ መድረክ አካሂዷል። የእንደራሴዎች ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያካሄዱት ይኸው የአስረጂ መድረክ፣ የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሚሆኑበትን አግባብ ለመደንገግ በወጣ ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ ነበር። ኹለቱ ቋሚ ኮሚቴዎችም፣ ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታቸዋል ከተባሉት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ አከናውነዋል። በግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኩ ላይ የተገኙት በፍትሕ ሚኒስቴር አማካሪ ሚኒስትር የሆኑት ዶ.ር. ታደሰ ካሳ፣ ረቂቅ አዋጁ የያዘውን ይዘት እና አጠቃላይ ፍሰት በዝርዝር አቅርበዋል። እንደ አማካሪ ሚኒስትሩ ገለጻም፣ ረቂቅ አዋጁ በዋናነት ከስድሳ አምስት ዓመታት በፊት የወጣውን የፍትሓ ብሔር ድንጋጌ፣ የባሕር ማዶ ሰዎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ እንዳይሆኑ የሚከለክለውን አንቀጽ የሚቀይር ነው። የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሐና አርአያሥላሴ በበኩላቸው፣ ረቂቅ አዋጁ አዋጅ ሆኖ በሚወጣበት ወቅት የውጭ ዜጎች እምነት ኖሯቸው ሀብታቸውን እንዲያፈሱ ለማበረታታት እና በአገሪቱ ውስጥ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን የማሳለጥ አላማን የሚያሳካ ስለመሆኑ አብራርተዋል። ሚኒስትር ሐና በዚኹ ማብራሪያቸው፣ ረቂቅ አዋጁ የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሚሆኑበትን አግባብ በመኖሪያ ቤት ላይ ብቻ መሆኑን እና የቤት ግዢውም ሆነ ሌሎች የአገልግሎት ሂደቶች የሚከናወኑት በውጭ ምንዛሪ እንደሚሆን መናገራቸውን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ዘገባ ጠቅሷቸዋል። ለዚኽም እነዚኹ የባሕር ማዶ ዜጎች፣ አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ዶላር የመነሻ ካፒታል መያዝ እንደሚጠበቅባቸው ሚኒስትር ሐና ተናግረዋል።

በዚኹ የአስረጂ መድረክ ላይ የተገኙት የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዋ ሄለን ደበበ በበኩላቸው፣ በአገራችን እየተስተዋለ ያለውን የቤት ፍላጎት እና አቅርቦት ክፍተት ለመመለስ ለውጭ ዜጎች በከፍተኛ ክፍያ የሚሸጥበት መንገድ ሲያድግ በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደረውን የኅብረተሰብ ክፍል ለመደጎም የሚያስችል አውድ ይፈጠራል ብለዋል። ሌላይኛው የአስረጂ መድረኩ ሰው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳ ቦሩ፣ ረቂቅ አዋጁ የውጭ ምንዛሬን የሚያመጣ፣ ለሪል ስቴት መስፋፋትም አስተወጽዖ የሚኖረው እና ለአገር የኢኮኖሚ እድገትም ጠቃሚ ነው ሲሉ ተደምጠዋል። የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት የሚሆኑበት አግባብ ሲፈቀድ፣ አገሪቷ ልታሳካ ያሰበቻቸው ዝርዝር ዓላማዎች በአዋጁ ውስጥ በአግባቡ ሊብራሩ እንደሚገባ ያሳሰቡት ደግሞ፣ የምክር ቤቱ የከተማ፣ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕ/ር መሐመድ አብዶ መሆናቸውን ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

# የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የተለያዩ የፌዴራሉ የመንግሥት ተቋማት፣ ተጠሪ ለሆኑባቸው የተለያዩ የሕዝብ ተወካዮች የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከዘጠኝ እስከ ዐሥር ወራት የሚሸፍነውን የሥራ አፈፃፀማቸውንም ሪፖርት በወርኃ ግንቦትም አቅርበው ነበር።

## የተቋማት ሪፖርቶች

በዚኹ ወር ለሕዝብ ተወካዮቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን ካቀረቡት ተቋማት መካከል፣ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊሲ ኮሚሽን አንዱ ነበር። የኮሚሽኑን የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን የገመገመው ቋሚ ኮሚቴውም፣ የፖሊስ ኮሚሽኑ የተለያዩ አገር ዓቀፍ እና ዓለም ዓቀፍ ስብሰባዎች፣ ሕዝባዊ እና ሃይማታዊ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ እና ግጭቶች እንዳይፈጠሩ በብቃት በመቆጣጠር ረገድ የተሰሩት ሥራዎች አበረታች እንደሆኑ ገልጿል። እንደ ምክር ቤቱ ዘገባ፣ በየጊዜው የሚከሰቱ ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ ለመምጣታቸው የኮሚሽኑ አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ቋሚ ኮሚቴው ጠቁሟል። የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳ ቦሩ፣ ከዚህ በፊት ያልነበረ የጀግኖች ማዕከል፣ የቀድሞው ፖሊስ አባላት እና የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደሪያን የመሳሰሉት መመሪያዎችን በተመለከተ የተሰራው ሥራ ሊበረታታ እንደሚገባ ገልጸዋል። ከዚኽ በተጨማሪም ምክትል ሰብሳቢው፣ በወንጀል መከላከል ብዙ ሥራዎች የተሰሩ ቢሆኑም አኹንም ፀረ-ሰላም ኃይሎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ ወንጀሎች እየፈጸሙ በመሆናቸው ወንጀልን ለመከላከል እና የወንጀል ሥጋትን ለመቀነስ የፖሊስ ኃይሉ ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመሆን የተጀመረውን ሕግ የማስከበር ሥራ ይበልጥ አጠናክሮ መሥራት እንዳለበት አበክረው መናገራቸው ተሰምቷል። ከዚኽ ባለፈም፣ የኮሚሽኑ የበጀት አፈጻፀም ስድሳ አምስት በመቶ ብቻ በመሆኑ በቀጣይ ሊታይ ይገባልም ብለዋል። የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገብረሚካኤል በበኩላቸው፣ በአዲስ አበባ እና በመላው አገሪቱ ያሉ 613 ከፍተኛ የመሠረተ-ልማት እና የፌደራል ተቋማት ላይ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ማንኛውንም ዓይነት ጥቃት እንዳያደርሱ በቂ የሰው ኃይል በመመደብ እና የ24 ሰዓት ጥበቃ በማድረግ ደህንነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ እንደተሰራ ማብራራታቸው ተዘግቧል። ኮሚሽነሩ በፀረ-ሰላም ኃይሎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅና የማረጋገጥ ተግባራትን የሚመሩት ኮሚሽን ማከናወኑንም ለቋሚ ኮሚቴው አብራርተዋል።

በእንደራሴዎች ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የፌደራል የሕግ እና ፍትሕ ኢንስቲትዩትን የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን የገመገመበት ደግሞ ኹለተኛው የፌደራል ተቋም ቁጥጥር ክንውኑ ነበር። ለቋሚ ኮሚቴው የተቋማቸውን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አምባሳደር ደግፌ ቡላ ሲሆኑ፣ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ እና አባላቶቹ የኢንስቲትዩቱን የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈፃፀም አስመልክተው ማብራሪያ ያሻቸዋል ያሏቸውን ጥያቄዎች አንስተዋል። የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ ምትኩ ማዳ፣ ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመናበብ እንደሚያከናውን ጠቅሰው፣ የሕዝብ ተዓማኒነትን ያረጋገጡ የፍትሕ ተቋማት እንዲኖሩ በዕቅድ ተይዞ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ለኮሚቴው አባላት አብራርተዋል።



የተከበሩ አቶ ኢሳ ቦሩ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ዳኛ አበበ ሰለሞን በበኩላቸው፣ በአዲሱ አዋጅ መሠረት ኢንስቲትዩቱ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ መሆኑ በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ የክህሎት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የፍትሕ መረጋገጥ ሂደት እና ውጤት ላይ ትልቅ ሚና አለው ብለዋልም። የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳ ቦሩ በበኩላቸው፣ ኢንስቲትዩቱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በብቃት ከመወጣት አኳያ በቅርብ የፀደቀውን የኢንስቲትዩቱን ማቋቋሚያ አዋጅ በተፋጠነ ጊዜ ወደ ተግባር መተርጎም እንደሚገባ አሳስበዋል።

ለኮሚቴው አባላት ማብራሪያ የሰጡት ዳይሬክተሩ ደግፌ ቡላ በተራቸው፣ የዳኞችን፣ የአቃቢያነ-ሕግ እና የመርማሪ ፖሊሶችን ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመላካከት በማሳደግ የሕዝብን እርካታ ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት እና ከክልሎች ጋር በጥምረት እየተሰራ መሆኑን መናገራቸው ተዘግቧል።

በወርኃ ግንቦት፣ በሦሥተኛነት የዘጠኝ ወር የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቱን የማቅረብ ተራው የቱሪዝም ሚኒስቴር ነበር። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን ሪፖርት ያደመጠው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

እንደ አገር በተደረገው ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያ ከተለዩት አምስት የኢኮኖሚ ምሰሶዎች መካከል አንዱ የሆነውን የቱሪዝም ዘርፍ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት እንደሚገባ አስገንዝቧል። የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አይሻ ያሕያ፣ ኢትዮጵያ ባላት የቱሪዝም ሀብት በአግባቡ ተጠቃሚ መሆን እንድትችል ነባር እና አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎችን ማልማት እንደሚገባ ለተቋሙ ተወካዮች አሳስበዋቸዋል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ካከናወናቸው ዋንኛ ተግባራት መካከል፣ በነባር ቅርሶች ላይ ጥገና ማድረጉ፣ እና ኹለት ቅርሶችን በዩኒስኮ ማስመዝገብ መቻሉ በጥንካሬ የሚታዩ አፈጻጸሞቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሳ በበኩላቸው፣ የጎብኚዎችን ፍሰት ለመጨመር የቱሪዝም መጠቆሚያዎች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰው፣ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎችም ዕሴት ተጨምሮባቸው እየለሙ መሆኑን ተናግረዋል። ሚኒስትሯ፣ በዘጠኝ ወራት ውስጥ ከ85 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች በዘርፉ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ጠቅሰው፣ ከ942ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎችም ሪፖርታቸው በሸፈናቸው ወራት ውስጥ ኢትዮጵያን መጎብኘታቸውን ጠቅሰዋል።

የወሩ መገባደጃ ላይ የዐሥር ወራት የዕቅድ አፈፃፀሙን ከምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር ለመወያየት የተጠራው ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር ነበር። ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት፣ ባለፉት ዐሥር ወራት ከግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ የተገኘው ገቢ ከ3 ቢሊየን ዶላር መሻገሩን ያነሱት የግብርና ሚኒስትሩ ዶ.ር. ግርማ አመንቴ፣ ከዚኽ ውስጥም ከ400 ሺህ ቶን በላይ ቡና ለውጪ ገበያ በመላክ 2 ቢሊየን ዶላር መገኘቱን ለቋሚ ኮሚቴው ገልጸዋል። ከዚኽ ባለፈም ፍራፍሬ፣ አበባ፣ ቅመማ ቅመም፣ እንስሳት እና የእንስሳት ውጤቶች ገቢ ከተገኘባቸው የግብርና ምርቶች ውስጥ ይገኛሉ። በዘንድሮው ዓመት በግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ የተገኘው ውጤት እንዲቀጥል ከአልሚዎች የሚነሱ የሎጀስቲክስ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ እና የመልካም አሥተዳደር ችግሮች ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን መፍታት እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው ማሳሰቡ ተዘግቧል። የኮሚቴው ሰብሳቢው የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ፣



የሕግና ፍትሕ ኢንስቲትዩት በውይይት ላይ

ለቀጣዩ ምርት ዘመን እየተደረገ ያለው የመሬት እና የግብዓት ዝግጅት አበረታች ኹኔታ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል። ሰሎሞን አክለውም፣ ወደ አገር ውስጥ የገባውን የአፈር ማዳበሪያ በአፋጣኝ ወደ አርሶ አደሩ የማድረስ እና ሥርጭት ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል። በግብርናው ክፍለ-ኢኮኖሚ በኩል ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያውን ለመደገፍ በምክር ቤቱ የጸደቁ አዋጆችን በመመሪያ በመደገፍ ወደ ሥራ በማስገባት የዘርፉን እድገት ማፈጠን ይገባልም ብለዋል። ለቀጣዩ የምርት ዘመን 24 ሚሊየን ቶን የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ወቅቱን ጠብቆ ተፈፅሟል ያሉት ሚኒስትር ግርማ በበኩላቸው፣ 12 ሚሊየን ኩንታሉ ለክልሎች ደርሷል ብለዋል። በአረንጓዴ አሻራ የደን ልማት ከ7 ቢሊየን በላይ ችግኞች መዘጋጀታቸውን ያነሱት ግርማ፣ 500 ሚሊዮን የሚሆኑት ቀድመው መተከላቸውን እና ከዚኽ ውስጥ 3.5 ቢሊየን የሚሆኑት ጥምር ጥቅም የሚሰጡ ችግኞች መሆናቸውን መናገራቸውን ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የተገኘው ዘገባ ያሳያል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በግንቦት ወር የገመገመው የፌደራል ተቋማቱን የዘጠኝ ወራት ተቋማዊ ቁመና ብቻም ሳይሆን፣ በሥሩ ያሉ የዲሞክራሲ ተቋማት ለ2018 ዓ.ም. ያቀረቡትን የበጀት ጥያቄም ነበር። በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚኹ ጉዳይ ላይ የተወያየው፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት ከመጡ የሥራ ኃላፊዎች ጋር መሆኑን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል። ቋሚ ኮሚቴው፣ የተቋማቱን የበጀት አጠቃቀምም ሆነ የበጀት ማስተካከያ የተደረገላቸውን እንዲኹም ገንዘብ ሚኒስቴር ለ2018 በጀት ዓመት ያስቀመጠውን የበጀት ጣሪያ እና ተቋማቱ ያቀረቡትን የበጀት ጥያቄ አስመልክቶ ማብራሪያ ጠይቋልም። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ በመደበኛውም ሆነ በካፒታል በጀት የሚቀርቡ የበጀት ጥያቄዎች የተጋነኑ እንዳይሆኑ ፍትሓዊ እና በመረጃ የተደገፉ ሊሆኑ እንደሚገባ መግለፃቸው ተጠቅሷል።

የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት ጥያቄን በሚመለከት ተቋማቱ ከስትራቴጂክ ዕቅዶቻቸው ጋር ለማስተሳሰር መሞከራቸውን በጠንካራነት ያነሱት ሰብሳቢው፣ ነገር ግን ለእያንዳንዱ የበጀት ዓይነት የተጠየቀው የገንዘብ መጠን በቁጥር ሊቀመጥ እንደሚገባ አመላክተዋልም። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝደንት ክብርት አበባ እምቢ አለ በበኩላቸው፣ ከአገራዊ የድጎማ ማሻሻያዎች እና ከአዲሱ መዋቅር ጋር ተያይዞ የተደረገው ጭማሪ፣ የበጀት መጠናቸውን ከፍ እንዳደረገባቸው ለኮሚቴው አባላት አብራርተዋል።

## ውጭ ጉዳዩ እንዴት ከረመ?

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ግንቦት አስፈጻሚውን በተመለከተ ያከናወኗቸው የሁለት ሚኒስትሮችን ምላሽ እና ማብራሪያዎችን ማዳመጥ ሲሆኑ፣ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ.ር. ኢ/ር ሀብታሙ ኢተፋ በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያን አኹናዊ የውጭ ጉዳይ አጀንዳን አንስቶ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቲዎስ ምላሽ እና ማብራሪያዎችን ያገኘበት ውሎም ነበር። በምክር ቤቱ 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 34ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የተገኙት ሚኒስትሩ፣ ኤርትራን ጨምሮ ከተለያዩ የጎረቤት አገራት ጋር ያለው አኹናዊ ግንኙነት፣ በድንበር አከባቢ የሚሰፍሩ የጎረቤት አገራት ሕዝቦች እና በውጭ ኃይሎች የተያዙ የኢትዮጵያ ግዛቶችን የተመለከቱት ጥያቄዎች ከእንደራሴዎቹ በኩል ተነስተውላቸው ነበር። ኢትዮጵያ ለጎረቤት አገራት ቅድሚያ የመስጠት ዲፕሎማሲያዊ መርህ እንዳላት ያነሱት ጌዲዮን፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኤርትራ ጋር የቃላት ጦርነት ውስጥ አልገባም ሲሉም፣ እንደራሴዎቹ በኤርትራ ጉዳይ ላነሱት ጥያቄ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን በመወከል ንግግር የሚያደርጉ ተቋማት እንዳሉ ያመለከቱት ጌዲዮን፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዜጎች፣ የሕዝብ ተወካዮች እና የቀድሞ የመንግሥት ኃላፊዎች የራሳቸውን ምልከታ እንደሚያነሱ የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ እነዚኽ አካላት ጆሮ ሊሰጣቸው ይገባል ሲሉም አሳስበዋል። እንነጋገር ብንል ብዙ የሚያነጋግር ነገር አለ ሲሉ የተደመጡት ሚኒስትሩ፣ ጉዳዩ መመራት ያለበት በጊዜው እና በጥንቃቄ እንደሆነም ለእንደራሴዎቹ አስረድተዋል። በኤርትራ በኩል ትንኮሳ ቢኖርም፣ አንዳንዴ በሆደሰፊነት፣ አንዳንዷን ደግሞ በራሱ በዲፕሎማቲክ ቻናል የሚመለሰውን ለመመለስ ጥረት እናደርጋለን ሲሉም መሥሪያ ቤታቸው እየሄደበት ያለበትን ሂደት ለምክር ቤቱ አባላት አብራርተዋል።

በባሕር በር ሰሞነኛ ጉዳይ ላይም የተናገሩት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ ስትራቴጂክ የሆኑ አገራዊ ጉዳዮችን ስታነሳ ትኩሳታቸው የሚጨምሩ አገራት አሉ ሲሉም ተደምጠዋል። ያም ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞቿን በተመለከተ ያላትን አቋም አጠናክራ እንደምትቀጥል ለእንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል። ግድብ ስንገነባ ያለ እኛ ቡራኬ እንዴት ይገነባል የሚሉ ነበሩ ያሉት ጌዲዮን፣ ያ ሳያስቆመን ግድቡን እንዳጠናቀቅነው ኹሉ፣ ሌሎች



ዶ.ር. ጌዲዮን ጢሞቲዎስ ምላሽ እና ማብራሪያዎችን ሰሲጡ

ፕሮጀክቶቻችንንም እውን ማድረጋችን አይቀርም ሲሉ ለፓርላማ አባላቱ ተናግረዋል። የባሕር በር ጥያቄን ለማሳካት የተጀመረው ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ እውን እስኪሆን ድረስ በዓለም ዓቀፍ ሕጎች እና በሰጥቶ መቀበል መርህ መሥራት ይገባል ከማለታቸው ባለፈ፣ የባሕር በር የማግኘት ጥያቄውን ዓለም ዓቀፍ አጀንዳ ማድረግ ያስቻለ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ሥራ መሰራቱንም ሲያብራሩ ተደምጠዋል። ኢትዮጵያ ጥቅሟን የምታስከብረው የጋራ ተጠቃሚነት መርህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እና የዓለም ዓቀፍ ሕግ አሰራር መርሆዎችን ከግንዛቤ ባስገባ መንገድ እንደሆነም ሚኒስትሩ ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል።

ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጌዲዮን ጢሞቲዎስ፣ በዚያ የምክር ቤት ውሏቸው በእነዚኽ ጉዳዮች ብቻም ሳይሆን፣ እስከዛሬ ኢትዮጵያ ባላካለለቻቸው ድንበሮች ዙሪያም ማብራሪያ ሰጥተው ነበር። ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር የምትዋሰንባቸውን በሺ ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠር ድንበርን የማካለል ሥራ ተቋማዊ ቅርጽ ሰጥቶ ለማከናወን በዝግጅት ላይ መሆኗንም ተናግረዋል። አገሪቱ ካላት ድንበር ውስጥ በአግባቡ የተሰመረ እና የተለየው ከሃምሳ በመቶ በታች መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሩ፣ ከአብዛኞቹ ጎረቤቶች ጋር ያለው የድንበር ጉዳይ ተጨማሪ ሰፊ ሥራ የሚፈልግ መሆኑንም ጠቁመዋል። የድንበር ጉዳይን በተመለከተ ከየአገራቱ ጋር ያሉትን ጉዳዮች የማላነሳው በምክንያት ነው ሲሉም መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

## የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ወርኃ ግንቦትን ያጠናቀቀው ሕግጋትን በማውጣት እና የተቋማትን ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም አይደለም፤ ከዚያ ተሻግሮም ከደርዘን በላይ የሚሆኑ ተቋማትን በተለያዩ የቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ሲጎበኝ፣ ከሦሥት ዐሥርት በላይ የሚሆኑ የመስክ ጉብኝቶችንም አድርጓል።

## የተቋማቱ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ በወከሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎቻቸው በኩል ከጎበኟቸው የፌድራል ተቋማት መካከል፣ በቀዳሚነት ማሳያ ሊሆን የሚችለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው። ግንቦት 14፣ 2017 ዓ.ም. ወደ ምርጫ ቦርዱ የተጓዙት የምክር ቤቱ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ሰፋ ያለ ምልከታ አድርገዋል። በምልከታቸውም፣ ቦርዱ ቀጣዩን ሰባተኛ ዙር አገራዊ ምርጫ ለማሳካት በሰው ኃይል፣ በጀት እና ግብዓት ረገድ ጠንከር ያለ ተቋማዊ ማሻሻያ ማድረግ እንዳለበት የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አዝመራ አንዴም በኩል አበክሮ አስገንዝቧል። ከዚህ ባለፈም፣ ቦርዱ ምርጫን አስመልክቶ የሲቪክ ማኅበራትን እና የሚዲያዎችን ዐቅም በመገንባት የዴሞክራሲ ልምምድ እንዲዳብር መሥራት እንደሚገባውም አዝመራ ጠቁመዋል፡፡ ዜጎች የዴሞክራሲ ግንዛቤያቸው እና ግዴታቸውን በአግባቡ እንዲረዱ የሥነ-ዜጋ የመራጮች ትምህርት መስጪያ የመረጃ ኅትመት በተለያዩ ቋንቋዎች ተዘጋጅተው መሰራጨት እንዳለባቸውም፣ ቦርዱን የጎበኙት የኮሚቴው አባላት ገልጸዋል፡፡ የቦርዱ አመራሮች በበኩላቸው፣ በቂ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ባለመኖራቸው ሰዎች አቤቱታቸውን ለማቅረብ ከስድስት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ ተጉዘው እንደሚመጡ ጠቅሰው፣ ተጨማሪ ጽሕፈት ቤቶች እንዲከፈቱ ቋሚ ኮሚቴው እገዛ እንዲያደርግላቸው ጥያቄያቸውን ማቅረባቸውም ተሰምቷል። የ2018ቱን አገራዊ ምርጫ ለመከወንም ከወዲኹ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙ የቦርዱ ኃላፊዎች ለኮሚቴው አባላት አብራርተዋል።

እንደራሴዎቹ በወሩ ሊጎበኙት የፈቀዱት ሌላኛው ፌደራላዊ ተቋም፣ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ነበር። ወደ ግንቦት መገባደጃ ላይ፣ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት የደረሱት በምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በተቋሙ የተከናወኑ ዋና ዋና የማሻሻያ ሥራዎችን ተመልክተው፣

ማሳሰቢያ ያሉትንም ጨምረው ለተቋሙ ኃላፊዎች እንደነገሯቸው የምክር ቤቱ ዘገባ ያትታል። የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወደጄ፣ ተቋሙ በሰው ኃይል ዐቅም ግንባታ እና ምቹ የሥራ ከባቢ መፍጠርን ጨምሮ፣ በተቋማዊ ማሻሻያው ያከናወናቸው ዋና ዋና ለውጦች ለሌሎች ተቋማት ተምሳሌት የሚሆን ነው ብለዋል። ደሳለኝ፣ መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል በነበረበት የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢ የእርምት እርምጃ መውሰዱን ሲናገሩ፤ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም ዓለማየሁ ደግሞ፣ የተቋሙ አመራሮች እና ሠራተኞች ተናበው በመሥራት አበረታች ለውጥ ማምጣታቸውን ጠቁመዋል። የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. በከር ሻሌም፣ የሚመሩት ተቋም በዚኹ ቋሚ ኮሚቴ ቀደም ሲል ተጎብኝቶ የተሰጣቸውን አስተያየቶች እንደግብዓት በመውሰድ ያከናወኗቸውን የለውጥ ሥራዎች በዚያ ለተገኙት የኮሚቴው አባላት ማብራራታቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል። ዳይሬክተሩ ለጥቀውም፣ በቀጣይ ተቋማቸው በዋናው መሥሪያ ቤት የጀመረውን የለውጥ ሥራዎች ወደ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶቹም ለማውረድ እንደሚሰራ ላገኟቸው እንደራሴዎች ነግረዋቸዋል።

በወርኃ ግንቦት በእንደራሴዎቹ የመጎብኘት ዕጣ የገጠመው ሌላይኛው ተቋም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነበር። ዩኒቨርሲቲውን የመጎብኘቱን አስፈላጊነት ያነሱት፣ በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢዋ ዶ.ር. ቤተልሔም ላቀው፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ሆኖ በተቋቋመበት አዋጅ መሠረት በ2016 ዓ.ም. ወደ ትግበራ ከገባ በኋላ አኹን ላይ የደረሰበትን ደረጃ መመልከት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዝደንት እና ከፍተኛ አመራሮች ጋር የተወያየው ኮሚቴው፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ በመሆኑ ያገኛቸው ጥቅሞች እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንም ማንሳቱ ተዘግቧል። ውይይቱም በተማሪዎች ቅበላ፣ የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ፣ በጥናትና ምርምር፣ በገንዘብ ምንጮች እና አሥተዳደር ጭምር ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ እንደነበር ታውቋል። በዚኽም፣ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዝደንት ዶ.ር. ሳሙኤል ክፍሌ፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ከሆነ ጀምሮ አዲስ አደረጃጀትን እና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ከማውጣት ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርተውላቸዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባላት በዩኒቨርሲቲው አፈፃፀም ዙሪያ ማብራሪያ የሚሹ ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን፣ ፕሬዝደንቱ እና ባልደረቦቻቸው ምላሽ እና ማብራሪያ ተሰጥተዋቸዋልም።



ጉብኝት በኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት

## የመስክ ጉብኝቶች

ግንቦት ሲብት ወደ ደቡብ የሄዱት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ዞን እና ቀቤና ልዮ ወረዳ ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች አፈፃፀማቸው ምን እንደሚመስል የመስክ ምልከታ በማድረግ ገምግመዋል። የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፈቲህ ማህዲ፣ ከዚኽ ቀደም ተፈጥሮ የነበረው የሰላም መደፍረስ መፍትሔ እንዲያገኝ ቋሚ ኮሚቴው ክትትል እና ድጋፍ ከሚያደርግላት የሰላም ሚኒስቴር መረጃ ማግኘቱን አስታውሰዋል። ያም ሆኖ የአካባቢው ሕዝብ ችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዳልተሰጠው በሕዝብ ውክልና ሥራ ወቅት ጥያቄ በማቅረቡ፣ ጉዳዩን በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ በማስፈለጉ ቋሚ ኮሚቴው ምልከታ ማድረጉን ጠቁመዋል። የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ዜጎች ስጋታቸው ተወግዶ ወደ መደበኛ ሕይወታቸው መግባት እንደሚጠበቅባቸው በማስታወስ፣ የተቸገሩ እና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ካሉ የፌዴራል መንግሥት ማገዝ የሚገባውን እንደሚያግዝ መናገራቸውን ከመስክ ምልከታው የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ከዚኽ ባለፈም፣ የመጣው ሰላም ዘላቂ እንዲሆን የተጀመሩት ጅምር ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል። በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የጉራጌ ዞን ዋና አሥተዳዳሪ ላጫ ጋሩማ እና የቀቤና ልዮ ወረዳ አሥተዳዳሪ ሙሳ ኢዶሳ በየበኩላቸው፣ አካባቢውን ወደ ሰላም ለመመለስ ባለፉት ጊዜያት የተሰሩ ሥራዎችን እና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እና በቀጣይም ሊፈቱልን ይገባል ያሏቸውን ጉዳዮች ጨምረው፣ አኹናዊ የሰላም ኹኔታው ምን እንደሚመስል ለቋሚ ኮሚቴው በዝርዝር ማቅረባቸውን ከመስክ ምልከታው የተገኙት መረጃዎች ያሳያሉ።

በጠቀስነው ግንቦት ወር በእንደራሴዎቹ የመጎብኘት ዕድል ካገኙት የመስኖ ልማት ግድቦች መካከል፣ የጊዳቦ የመስኖ ልማት ግድብ ይገኝበታል። በሲዳማ ክልል እና በምዕራብ ጉጂ ኦሮሚያ ክልል አዋሳኝ ላይ በ1.6 ቢሊዮን ብር ወጪ የተገነባውን ይኽንን ግድብ የጎበኙት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ። አባላቱም፣ የግድቡን ቀሪ የካናል ሥራዎች በማጠናቀቅ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ አሳስበዋል። በ2002 ዓ.ም. ተጀምሮ በ2011 ዓ.ም. ውኃ መያዝ መቻሉ የተጠቀሰው የግድቡ ሥራ ቢጠናቀቅም፣ በሲዳማ ክልል በኩል መገንባት ከነበረበት 12.8 ኪሎ ሜትር የውኃ መተላለፊያ ካናል ውስጥ 400 ሄክታር ብቻ የሚያለማ 2.5 ኪሎ ሜትር ካናል ብቻ መገንባቱ ሲታወቅ፤ በኦሮሚያ ክልል በኩልም፣ መሠራት ከነበረበት 12.2 ኪሎ ሜትር ካናል ውስጥ 8.6 ኪሎ ሜትር ብቻ መገንባቱ ተነግሯል። በሲዳማ ክልል ከ5000 በላይ የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን ወጣቶች፣ ባለሀብቶች እና በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማደራጀት በእርሻ ሥራዎች ለማሰማራት መታቀዱን እዚያ ለደረሱት የቋሚ ኮሚቴው አባላት ያብራራቱ ደግሞ




የክልሉ ውኃ፣ ማዕድን እና ኤነርጂ ቢሮ የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ አስተባባሪው ሙሉጌታ ጳውሎስ ነበሩ። ፕሮጀክቱ በፌደራል መንግሥት የሚገነባ መሆኑን ጨምረው የገለፁት ኃላፊው፣ በክልሉ የሚገኝ ሜጋ ፕሮጀክት በመሆኑ ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል እያደረግን እንገኛለን ሲሉ ለኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል። የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ካሊድ አባመጫ በበኩላቸው፣ ከፍተኛ የአገር ሀብት የፈሰሰበትን ጊዳቦ መስኖ ልማት ግድብን ወደ ሀብት ለማስገባት ኦሮሚያ ክልል የሚነሱ የይዞታ ባለቤትነት ጥያቄዎችን በመመለስ እና በሥፍራው የሚገኙ ነዋሪዎችን በማንሳት፣ ኹለቱም ክልሎች በቅንጅት መሥራት እንደሚገባቸው ማሳሰባቸውን ለመረዳት ተችሏል።

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ግንቦት ወር ውስጥ ካደረጓቸው የመስክ ምልከታዎች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው ሌላው ጉብኝታቸው፣ በድንበርተኛዋ ክልል ጋምቤላ ያደረጉት የመስክ ጉብኝት ነበር። በክልሉ የሚገኘውን ጆዊ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያን የጎበኙት የምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በመጠለያ ጣቢያው ውስጥ የሚሰጡ የተለያዩ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ተዘዋውረው ተመልክተዋል። በምልከታቸውም፣ ለስደተኞቹ የዕለት ተዕለት አገልግሎት የሚሰጡትን ተቋማት ዐቅም በማሳደግ በዚያ ለተጠለሉት የጎረቤት አገራት ዜጎች የተሟላ መሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚያስፈልግ ገልጸዋልም። በአካባቢው የስደተኞችን ሰላም እና ደኅንነት ለማረጋገጥ የተሰሩት ሥራዎች አበረታች ናቸው ያሉት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነገዎ፣ በመጠለያ ጣቢያው የትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በማስፋት ረገድ በርካታ ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም የበለጠ ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው ማሳሰባቸውም ተመላክቷል። በአኹኑ ወቅት በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ባለው ተለዋዋጭ ፖለቲካዊ እና ጂኦ-ስትራቴጂካዊ ምክንያቶች የተነሳ፣ ሰዎች ከቀያቸው የሚፈናቀሉበት ምኅዳር ሰፍቷል ሲሉ የተደመጡት ዶ.ር. ዲማ፣ በዚህም ምክንያት አገራችን የተቀበለቻቸውን ስደተኞች ደኅንነት ተረጋግጦ እንዲኖሩ ከሚያስችሉ ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ተቀራርባ እየሰራች ትገኛለች ማለታቸውንም ከመስኩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት የጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው መዝገበወርቅ ገብረማርያም በበኩላቸው፣ በአኹኑ ወቅት የአሜሪካ መንግሥት በዕርዳታ ድርጅቶች ላይ በጣለው ማዕቀብ የተነሳ በስደተኞች ሰብዓዊ እና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ እዚያው ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት አስረድተዋል። በእርግጥ በዶ.ር. ዲማ የተመራው ቋሚ ኮሚቴው፣ ጋምቤላ ውስጥ የጎበኘው ይኸንን መጠለያ ጣቢያ ብቻ ሳይሆን በኩሌ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያንም ነበር። ከመጠለያ ጣቢያው ተወካዮች ጋር የተወያየውን ኮሚቴም የመሩት የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎዎ፣ በደቡብ ሱዳን ያለው ወቅታዊ አለመረጋጋት የስደተኞችን ቁጥር ከዚኽ በላይ ሊጨምረው እንደሚችል በመገመት፣ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ተቀራርበው መሥራት እንደሚገባቸው ገልፀዋል። ከደቡብ ሱዳን ተፈናቅለው ጣቢያው ውስጥ የተጠለሉት ስደተኞች በበኩላቸው፣ ከዚኽ በፊት ይደረግላቸው የነበረው የምግብ መጠን እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ እየቀነሰ በመምጣቱ ለችግር መጋለጣቸውን ለኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ ከዚኽ በፊት ለአንድ ወር ተብሎ ይሰጣቸው የነበረው 13 ነጥብ 5 ኪሎ ግራም ዱቄት ወደ 7 ኪሎግራም ዝቅ በማለቱ ለርሃብ መጋለጣቸውንም ለቋሚ ኮሚቴው ተናግረዋል። የስደተኞቹን ምሬት የተጋሩት የመጠለያ ጣቢያው ኃላፊ ቲያ ዴንግ ማር በበኩላቸው፣ ለችግሩ መባባስ የአሜሪካ መንግሥት በእርዳታ ድርጅቶች ላይ በያዘው አቋም ምክንያት መጠለያ ጣቢያው ላይ ይሰሩ የነበሩ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ የዕርዳታ ድርጅቶች ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱ እንደሆነ ገልጸዋል። ችግሮቹ በዚህ የሚቀጥሉ ከሆነ በቀጣይ ኹለት እና ሦሥት ወራት ምንም ዓይነት የምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች አቅርቦት ላይኖር ይችላል የሚል ስጋት እንዳደረባቸውም፣ በዶ.ር. ዲማ ለተመራው ኮሚቴ ጨምረው መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል።

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የ ኢፌዴሪ የአንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በዚኹ ግንቦት ወር ውስጥ አራት ፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ከውኗል። በቀዳሚነት የሚጠቀሰው፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን አስመልክቶ አንደራሴዎቹ ዛምቢያ ለላከችው ልዑክ የምክር ቤቱን ልምድ ያካፈሉበት ኹነት ነው።

እንደምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በተቀመጠው መሠረት የሕግ አወጣጥ፣ የማፅደቅ ሥርዓት እና አተገባበር ሂደትን አስመልክቶ የምክር ቤቱ አባላት እና የሥራ ኃላፊዎች ለልዑካን ቡድኑ አብራርተዋል። የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአንድ አገር ላይ በመደበኛ የሕግ ማስከበር ሂደት ማስከበር በማይቻልባቸው በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የሚተገበር መሆኑን፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩ ለዛምቢያዎቹ ተወካዮች አብራርተውላቸዋል። ምክትል ሰብሳቢው፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ምክር ቤቶች የመንግሥት ተግባራት እና የሰብዓዊ መብቶች መከበርን የመከታተል እና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል። ኢትዮጵያ በቅርብ ዓመታት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በታወጀባቸው ወቅቶች የተገኙ ልምዶች ለልዑካን ቡድኑ አካፍለዋል። ከኢትዮጵያ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሕግ አወጣጥ ሂደት ጠቃሚ ልምድ ማግኘታቸውን የልዑካን ቡድኑ አባላት መግለፃቸውን የጠቀሰው የምክር ቤቱ ዘገባ፣ በአፍሪካ አገራት መካከል ያለው ግንኙነት እና ልምዶችን በመቀመር በጋራ የመሥራት ባህል ሊጠናከር ይገባል ብለዋልም። ኢትዮጵያ ያካበተችው የአደጋ እና አስቸኳይ ጊዜን በሕግ የመምራት እና የማሥተዳደር ልምድ አስደናቂ መሆኑን አክልው መናገራቸውንም ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በዘጠነኛው የዓመቱ ወር ውስጥ ምክር ቤቱ የከወነው ሌላይኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ከአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ያደረጉት ምክክር ነበር። እንደ ምክር ቤቱ ዘገባ ከሆነም፣ በአውሮፓ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝደንት ዮናስ ኦማርጄ የተመራው ቡድን፣ ከአፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ጋር በኢትዮጵያ እና በቀጠናዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡ አፈ-ጉባኤውም፣ የኢትዮጵያ እና የአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ ቀደም ሲል የነበራቸውን ትብብር በማጠናከር፤ በቀጣይም በዲሞክራሲ ግንባታ እና በሰላም ዙሪያ በጋራ ለመሥራት ኢትዮጵያ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ለልዑካን ቡድኑ አስረድተዋል። የአውሮፓ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝደንት ዮናስ ኦማርጄ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ እያነሳች ያለችው የባሕር በር የባለቤትነት ጥያቄ ዓለም ዓቀፍ ሕግጋት መሠረት በሰላማዊ እና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ምላሽ ያገኝ ዘንድ የአውሮፓ ፓርላማ ፍላጎት መሆኑን መናገራቸው ተዘግቧል። የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽንም ስኬታማ ይሆን ዘንድ፣ የአውሮፓ ፓርላማ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ምክትል ፕሬዘዳንቱ ለአፈ-ጉባኤው አስረግጠውላቸዋልም።

በዚኹ ግንቦት ወር፣ የህንድ የፓርላማ ልዑክን ቡድን አባላትንም በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ያነጋገሩት የተከበሩ አቶ ታገሰ፣ በኹለቱ አገራት መካከል ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን በማንሳት በቀጣይ ወደተሻለ ደረጃ ማሳደግ በሚያስችሉ ኹኔታዎች ዙሪያ ከልዑክ ቡድኑ ጋር መወያየታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቁሟል። የአገራቱ ኹለንተናዊ ግንኙነት ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ መሆኑን ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ ኹለቱ አገራት በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ መድረኮች ላይ ብሔራዊ ጥቅማቸውን እና ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በጋራ እየሰሩ እንደሆነም ገልጸዋል። በምክር ቤቱ የውጭ ግኑኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል የተከበሩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው፣ በኹለቱ አገራት ቡድኖች መካከል የተደረገው ምክክር በትምህርት፣ አሸባሪነትን በጋራ በመዋጋት እና መዋዕለ-ንዋይን በማበረታታት ረገድ ትልቅ አበርክቶ እንዳለው አንስተዋል። የሕንድ የፓርላማ አባል እና የልዑካን ቡድኑ መሪ ሱፕሪያ ሱሌ፣ ኹለቱ አገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በጋራ እየሰሩ እንደሆነ አንስተው፣ በቀጣይም የአገራቱን የሕዝብ ለሕዝብ እና ኢኮኖሚዊ ግንኙነቶች ይበልጥ ለማጠናከር እንሰራለን ማለታችውን ዘገባዎቹ ጠቅሰዋቸዋል።



የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ከህንድ የፓርላማ ልዑክን ቡድን አባላት ጋር

*በዘጠነኛው የዓመቱ ወር ውስጥ ምክር ቤቱ የከወነው ሌላይኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ከአውሮፓ ኅብረት ፓርላማ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ያደረጉት ምክክር ነበር። እንደ ምክር ቤቱ ዘገባ ከሆነም፣ በአውሮፓ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝደንት ዮኖስ ኦማርጄ የተመራው ቡድን፣ ከአፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ ጋር በኢትዮጵያ እና በቀጠናዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርጓል፡፡*

የግንቦት ወሩ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አራተኛው ፓርላማ ተኮር ዲፕሎማሲ፣ አፈ-ጉባኤው በአንድ አህጉራዊ ጉባኤ ላይ መሳተፋቸውን የተመለከተው ነበር። “የማይበገር ማኅበረሰብ እና ጤናማ አካባቢ የሰው ኃይልን በብዛት የሚጠቀሙ የመዋዕለ-ንዋይ ፕሮግራም አካሄዶች” በሚል መሪ ሐሳብ፣ በአፍሪካ ኅብረት መሰብሰቢያ አዳራሽ፣ 20ኛው የዓለም ሥራ ድርጅት በሥራ ላይ የተመሰረተ የባለሙያዎች የተሰኘ አህጉራዊ ስብሰባ ተካሂዶ ነበር፤ በዚኹ ስብሰባ መክፈቻ መርኃ ግብር ላይ የተገኙት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ አቶ ታገሰ፣ ስብሰባው አፍሪካውያን ፖሊሲ አውጪዎች እና ባለሙያዎች ፈጠራን መሠረት ያደረገ ሥራ ለመፍጠር፣ ድኅነትን ለመቀነስ እና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም የሚያግዝ ነው ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይሄንን ለማሳካት ደግሞ በአህጉሪቱ የኹሉንም የጋራ ጥረት ይጠይቃል ያሉት አፈ ጉባኤው፣ ለዚህም ኢትዮጵያ ቁርጠኛ መሆኗን ተናግረዋል። የኢትዮጵያ የልማት ግቦች ለሥራ ፈጠራ ትኩረት የሚሰጡ ናቸው ያሉት ታደሰ፣ ድህነትን ለመቀነስ፣ የሥራ እድል ለመፍጠር እና ፍትሓዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸውም ብለዋል። አፍሪካን ከድህነት፣ ኋላ ቀርነት እና ከሥራ አጥነት የጸዳች ለማድረግ የጋራ ቁርጠኝነት ይጠይቃልም ማለታቸውን ዘገባዎቹ አስታውሰዋል።

# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው

የ ኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ግንቦት ወርን ያገባደደው ከላይ አጠር አድርገን የዳሰስናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን በመወጣት ብቻም ሳይሆን፤ አንድም የራሱን የዘጠኝ ወር አፈፃፀም በመገምገም፤ አንድም ለራሱ በተለይ ሴት እንደራሴዎች የዐቅም ማጎላመሻ ሥልጠና በመስጠት እና የሴት እንደራሴዎቹን ጠቅላላ ጉባኤ በማካሄድ ነበር።



በ ተጠቀሰው ግንቦት ወር፣ የምክር ቤቱ የ2017 ዓ.ም. በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ ክንውን፣ በምክር ቤቱ የአማካሪ እና አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት በጋራ መገምገሙን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። በግምገማው ላይ የተናገሩት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ምክር ቤቱ ሕግጋትን የሚያወጣበት ዋና አላማ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ከመሆኑ አንጻር፣ ሕግጋቱን ከማርቀቅ አስከ ማፅደቅ ባለው ሂደት ማኅበረሰቡ ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል እንደሚገባ ማስገንዘባቸው ተሰምቷል። ይኽንንም ከግብ ለማድረስ የምክር ቤቱን የአሰራር ሥርዓት ጊዜውን በመጠኑ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች በማስደገፍ ኅብረተሰቡ ቀጥተኛ ተሳታፊ እንዲሆን ለማስቻል የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸውም ብለዋል። ምክትል አፈ-ጉባዔዋ የተከበሩ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎች ወቅት ኅብረተሰቡ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደሚያነሳ ጠቅሰው፣ ምክር ቤቱም ለጥያቄዎቹ ተገቢውን ምላሽ በማይሰጡ እና ኃላፊነታቸውን በማይወጡ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እንደሚሰራ ተናግረዋል። በምክር ቤቱ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ በበኩላቸው፣ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ምክር ቤቱ ባከናወናቸው ሕግ የማውጣት፣ የክትትል እና ቁጥጥር፣ የውክልና እንዲኹም የፓርላመንታዊ የዲፕሎማሲ ሥራዎች የተገኙ ተጨባጭ ለውጦች የሚገመገምበት ሥርዓት በመዘርጋት፣ በቀጣይ የሚሰሩ ምክር ቤታዊ ሥራዎች የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ለማስቻል የሚያግዙ የተለያዩ የአሰራር ሥርዓቶች እንደሚዘጋጁ ጠቁመዋል። የቋሚ ኮሚቴዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ካቀዱት ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ አፈፃፀም ማሳየቱን ባቀረቡት የዘጠኝ ወራት የምክር ቤቱ የአፈፃፀም ሪፖርት ያተቱት ደግሞ፣ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ምክትል ዋና ጸሓፊ ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ ነበሩ። ዋና ጸሓፊው፣ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዘጠኝ ወራት አፈጻጸም ከ86 በመቶ በላይ መሆኑን ገልጸው፣ በቀጣይ በሥራ ላይ የታዩ ጥንካሬዎችን የበለጠ በማጠናከር ላይ እንደሚያተኩርም መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ፣ የሴት እንደራሴዎቹን ጠቅላላ ጉባኤም ያካሄደው በዚኹ ግንቦት ወር ነበር። በ2ኛው የሴት እንደራሴዎች ኮከስ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ እና የኮከሱ የበላይ ጠባቂ የተከበሩ ሎሚ በዶ፣ ሴቶችን በማብቃት በአገረ-መንግሥት ግንባታ ተሣትፏቸውን ለማሳደግ በትኩረት እንደሚሰራ ማስገንዘባቸውን ከጉባኤው የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ሠላም የመጀመሪያም የመጨረሻም ጉዳያችን ነው ያሉት ሎሚ፣ የኮከሱ አባላት አገራዊ ሠላምን ለማረጋገጥ ከመንግሥት ጎን በመቆም የበኩላቸውን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ ሊሆኑ እንደሚገባም ጠቁመዋል። የፌደራል መንግሥቱ ከታጠቁ ኃይሎች ጋር ለመደራደር ቁርጠኛ አቋም እንዳለው የጠቆሙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ፣ ኮከሱ የምክር ቤቱን ተልዕኮ ሲፈጽም የሠላም ጉዳይን ሊያተኩርበት እንደሚገባ ለሴት እንደራሴዎቹ ነግረዋቸዋል።

በጠቅላላ ጉባኤው በቀረበው የሦሥት ዓመት ከመንፈቅ የኮከሱ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን አስመልክቶም፣ በኮከሱ አባላት ሰፊ ውይይት ተደርጎበት በሙሉ ድምፅ መጽደቁን የጉባኤው መረጃ አመላክቷል። ከዚኹ ዜና ጋር በተያይዘም፣ እኒኹ የኮከሱ አባላት፣ ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ በተሰኘ ተቋም አማካኝነት ሥርዓተ ጾታ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ማግኘታቸው ተዘግቧል። የኮከሱ ሰብሳቢ የተከበሩ ኪሚያ ጁንዲም፣ ሥልጠና ሰጪው ፕላን ኢንተርናሽናል፣ ከኮከሱ ጋር በጋራ በመሆን የሥርዓተ ጾታ እኩልነት እንዲረጋገጥ የተሰሩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ሥራዎች አመረቂ ውጤት እንዳስገኙ ገልፀዋል።

# ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ግንቦት ወርን ያሳለፈው፣ አገሪቷ ከተለያዩ አገራት እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ያደረገቻቸውን የብድር ስምምነቶችንም በማጽደቅ ነበር።



የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ግንቦት ወርን ያሳለፈው፣ አገሪቷ ከተለያዩ አገራት እና ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር ያደረገቻቸውን የብድር ስምምነቶችንም በማጽደቅ ነበር።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ፣ በዚኹ ወር ባካሄደው 29ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ ኹለት የብድር ስምምነቶችን ማጽደቁን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጆቹን አስመልክቶ የመንግሥት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ መሠረት ኃይሌ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡ ሲሆን፣ አዋጆቹም በቀጥታ ወደ ኹለተኛ ንባብ በመሸጋገር ውይይት ተደርጎባቸው እንዲፀድቁ መተየቃቸውን ተከትሎ፣ እንደራሴዎቹ አጽድቀዋቸዋል። የብድር ስምምነቶቹን አስመልክቶ የምክር ቤት አባላት በርካታ ጥያቄዎችን እና አስተያየቶችን ያቀረቡ ሲሆን፣ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. እዮብ ተካልኝ ምላሽ እና ማብራሪያ መስጠታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል። በዚህም መሰረት በኢፌዲሪ እና በጣሊያን መንግሥት መካከል ለአካባቢያዊ እና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት የበጀት ድጋፍ ማስፈጸሚ ያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1377/2017 ሆኖ በሙሉ ድምፅ ፀድቋል። በተመሳሳይም በኢትዮጵያ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለመማር ማስተማር ማጎልበቻ የትምህርት ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚ ያ የተደረገውን የብድር ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1378/2017 ሆኖ በሙሉ ድምፅ መጽደቁን ይኸው የምክር ቤቱ መረጃ ጠቁሟል። ከእነዚኽ የብድር ስምምነቶ ባለፈ፣ በአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚ ያ ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1379/2017 ሆኖ በሦሥት ድምፀ- ተዐቅቦ በአብላጫ ድምፅ ይጸድቅ ዘንድ የእንደራሴዎቹ ፈቃድ ሆኗል። በመጨረሻም ምክር ቤቱ በዚኹ 29ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ በኢትዮጵያ መንግሥት እና በኦስትሪያ ፌዴራል መንግሥት መካከል የተፈረመውን የአየር ትራንስፖርት ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 1380/2017 ሆኖ በሙሉ ድምፅ ማጽደቁን የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ፣ ከሳምንታት በኋላ ባካሄደው 33ኛ መደበኛ ስብሰባውም፣ ሌሎቹ ኹለት የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል። በቀዳሚነትም፣ በኢትዮጵያ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል ለተቀናጀ የውጤታማ ግብርና ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ለወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚ ያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ አስመልክቶ ማብራሪያ ያቀረቡት፣ የመንግሥት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ነበሩ። ተጠሪ ሚኒስትሩም፣ የብድር ስምምነቱ በግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለማስፋፋት፣ የባለሙያዎችን ዐቅም ለመገንባት፣ የመስኖ አውታሮችና እና የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲኹም ወጣቶች በግብርና ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል ስምምነት መሆኑን ጠቅሰዋል። በዚኹ 33ኛ መደበኛ የእንደራሴዎቹ ስብሰባ ላይ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለሴቶች እና ልጃገረዶች ጤና የተቀናጀ፣ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የቀረበውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅን አስመልከቶም የቀረበውን ኹለተኛውን የብድር ስምምነትም እንዲኹ ለእንደራሴዎቹ ያብራሩት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ ነበሩ። ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው፣ ስምምነቱ በሴቶች ቅድመ-ወሊድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን ለመፍታት ብቻም ሳይሆን፣ ምቹ የጤና ተቋማትን ለመገንባት እና የጤናውን ዘርፍ ተደራሽ ለማድረግ ያለመ ስምምነት እንደሆነ አትተዋል።

# የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታዎች

## አዋጅ ቁጥር 1383/2017

6ኛው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ግንቦት 26 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 33ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ ከዐሥራ ስምንት ዓመታት በፊት ጸድቆ የነበረውን፣ አዋጅ ቁጥር 513/1999 የተሰኘውን አዋጅ አሻሽሏል። ምክር ቤቱ ያሻሻለው ይኽ አዋጅ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅ ሲሆን፣ አዋጅ ቁጥር 1383/2017 በሚልም በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል። ተቋማችንም፣ በወርኃ ግንቦት ከጸደቁት አራት ሕግጋት መካከል ይኽኑን አዋጅ አጠር አድርጎ ሊዳስሰው መርጧል።

### ማሻሻሉ ለምን አስፈለገ?

የቅጣት እና መሰል እርምጃዎችን አካቶ በድጋሚ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በሚል ከዐሥራ ስምንት ዓመታት በፊት የጸደቀውን ነባር አዋጅ ለማሻሻል ያስፈለገበትን ምክንያት፣ ለእንደራሴዎቹ የቀረበው የአዋጁ ማብራሪያ ጥቂት ነጥቦችን ያነሳል። እንደ ማብራሪያው ከሆነም፣ ነባሩን የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻል ያስፈለገው፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ተግባራትን ተከታትሎ ለማስፈጸም በማሰብ እንደሆነ ሰነዱ ያስረዳል። በሥራ ላይ ያለውን አዋጅ ለማሻሻል በምክንያትነት የተነሳው ሌላው ጉዳይ፣ ሕጉ በአገር ውስጥ የሚገኙ የፕላስቲክ ምርት አምራቾችን ለመቆጣጠር ምቹ አለመሆኑ ነው ይላል። አኹን በሥራ ላይ ባለው አዋጅ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የፕላስቲክ ምርቶች ውፍረታቸው ከ0.03 ሚሊ ሜትር በታች ብቻ መሆናቸውን የጠቀሰው ማብራሪያው፣ እነዚኽን ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ ማሻሻያው ማስፈለጉን አመልክቷል። የአዋጁ ማሻሻያ ገፋ አድርጎ እንደሚጠቅሰውም፣ በፕላስቲክ ምርት ላይ የሚሰጠው ፈቃድ ፕላስቲክ እና ጎማ ተብሎ በጠቅላላ የሚሰጥ መሆኑ፣ ለይቶ ለመቆጣጠር ከባድ እንዳደረገው ያነሳል። ከዚኽ አኳያም፣ በተለይ አገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች ላይ ተግዳሮት የሚያስከትል ነው ያለው ማብራሪያው፣ በነባሩ አዋጅ ስለፕላስቲክ ቆሻሻ የተደነገገው ማምረት ወይም ወደ አገር ማስገባት ብቻ መሆኑ እና ስለ አጠቃቀም ወይም አያያዝ በአግባቡ ያላካተተ መሆኑ የቁጥጥር ስርዓቱን ውጤታማ እንዳይሆን ማድረጉ የማሻሻያው መፍትዔ መሆኑን ጠቅሷል። ከዚኽ ባለፈም፣ በአገሪቷ የደረቅ ቆሻሻ አዋጅ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው ከዐሥራ ሦሥት ዓመታት በፊት ቢሆንም፣ የሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትሉ ተግባራትን ተከታትሎ ለማስፈጸም እና የሕግ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የተሟላ የሕግ ማዕቀፎች አለመኖሩም የማሻሻያው መነሾ ነው። በዚህም በነባሩ አዋጅ ከግለሰቦች እንስቶ እስከ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሊከተሉት የሚገባ አቅጣጫ ባለመቀመጡ አዲሱን አዋጅ ማውጣት ማስፈለጉን የሚመለከታቸው የመንግሥት ተጠሪ ባለሥልጣናት ሲናገሩ ተደምጠዋል።



በጥናት ላይ ተመስርቶ የተሰራ ነው የተባለው አዋጅ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚውሉ የፕላስቲክ ከረጢቶችን የሚመለከት እና ነዋሪዎች እና ፋብሪካዎች ደግሞ በአካባቢያቸው ላይ ያለውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ የተመለከተ ሲሆን፤ ነባሩ አዋጅ ዐሥራ ስምንት ዓመታትን ያስቆጠረ እንደመሆኑ፣ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ለገጠሩ የማኅበረሰብ ክፍል ብዙ ትኩረት ያልሰጠ መሆኑም ሌላይኛው ተጠቃሽ ምክንያት መሆኑ ተጠቅሷል። የከተሞች መስፋፋት እና ተያያዞ የመጣው የከተሜው ነዋሪ መብዛት ጉዳይም እንዲኹ ለአዋጁ መሻሻል በምክንያትነት ሲነሳ ተስተውሏል፤ እንደ ባለሥልጣናቱ ገለፃም፣ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሚመነጨው የቆሻሻ መጠን እየጨመረ መምጣቱን በነባሩ አዋጅ መምራት አልተቻለምና አዲስ አዋጅ ማዘጋጀት አስፈልጓል። የተሻሻለው አዋጅ፣ ለአካባቢ ብክለት የሚዳርጉ እና አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ምርቶች በሥነ-ምኅዳር ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መከላከል ዓይነተኛ አላማ መሆኑም ተነግሯል።

እነዚኽን እና ተያያዥ ክፍተቶችን ለማሻሻል የተዘጋጀው አዲሱ አዋጅ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ማምረት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ፣ ማከማቸት ወይም መጠቀምን ከልክሏል። የፕላስቲክ ከረጢት ማለት አነስተኛ ጥግግት ያለው፣ በቀላሉ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ እና ሌሎች ምርቶችን ለመያዝ የሚያገለግል እንደሆነም የተሻሻለው አዋጅ ብያኔውን አስቀምጧል። አዲሱ አዋጅ የፕላስቲክ ከረጢት የሚለውን አገላለጽ ጥቅም ላይ ያዋለው፣ በተለምዶ ፌስታል የሚባለውን ምርት ለማመላከት እንደሆነም፣ ከላይ የጠቀስነው የማሻሻያው መብራሪያ ሰነድ ጠቁሟል።

## ዋንኞቹ ነጥቦች

የተሻሻለው አዲሱ አዋጅ፣ የፕላስቲክ ከረጢት በሚያመርቱም ሆነ በሚጠቀሙ ግለሰቦች እና ተቋማት ላይም የወንጀል ተጠያቂነትን የዘረዘረ ነው። ለማሳያ ያህልም፣ ለእንጀራ፣ ለዳቦ እና ለተለያዩ የሸቀጥ እቃዎች መያዣነት የሚውለውን የአንድ ብሩን ፕላስቲክ ይዞ መገኘት ከ2,000 እስከ 5,000 ብር የሚያስቀጣ ሲሆን፤ ከዚኽ በተጨማሪም፣ ያመረተ ወይም ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ለገበያ ያቀረበ ወይም የሸጠ፣ ለንግድ ዓላማ ያከማቸ ወይም ይዞ የተገኘ ከ50,000 ብር በማያንስ እና ከ200,000 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ5 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ አዋጁ ያዝዛል፡፡ አዋጁ አጠቃላይ የደረቅ ቆሻሻን የሚመለከት ቢሆንም፣ በብዛት ያተኮረው ግን በፕላስቲክ ቆሻሻ ላይ ሲሆን፣ ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ዲዛይን ሲደረግ አንስቶ ምርቱ እስከሚወገድበት ድረስ ያለውን ተመልክቷል። ስድስት ክፍሎች እና ሃያ ስምንት አንቀጾች ያሉት አዋጁ፣ ሦስት መርሆዎች እንዳሉትም አስቀምጧል። የበከለን ማስከፈል የሚለው ቀዳኣሚው ሲሆን፣ ቆሻሻን ከምንጩ መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት ማድረግ እና በአግባቡ ማስወገድ እንዲኹም የኅብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ የሚሉት በኹለተኛነት እና በሦሥተኛነት የተቀመጡ መርሆዎች ናቸው።

በአዲሱ አዋጅ የተሻረው ነባሩ አዋጅ፣ በቀላሉ በስብሶ ወደ አፈር የሚደባለቅ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያልተደረገበትን የፕላስቲክ ከረጢት ለገበያ ማቅረብ ይከልክል ነበር። በሌላ በኩል አዲሱ አዋጅ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ማምረት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው የሚል ድንጋጌ ተካትቶበታል። የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና አወጋገድን በስፋት ያካተተው አዋጁ፣ የፕላስቲክ ጫማዎችን፣ የውኃ ኮዳዎችን እና ወፍራም የፕላስቲክ ውጤቶችን እንደማይጨምር ደንግጓል። አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክን የተመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች አፈጻጸምን መቆጣጠር እና ጥሰት ሲኖር ተገቢ የእርምት እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት የተሰጠው ደግሞ ለየአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ነው። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተሰጠው ኀላፊነት ይኽም ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮች እንዲመረቱ፣ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ በመመሪያ የመወሰን ሥልጣንም ጭምር ነው።

ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቤት ይዞታው ድንበር አንስቶ ቢያንስ እስከ ሀያ ሜትር ባለው ርቀት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን የማጽዳት ኃላፊነት እንዳለበት የሚደነግገው አዲሱ አዋጅ፣ የአገልግሎት መስጫ እና የንግድ ተቋማት ደግሞ እስከ ሃምሳ ሜትር ርቀት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን የማጽዳት ኃላፊነትን ጥሎባቸዋል። የፕላስቲክ አምራቾቹን አስመልክቶም ድንጋጌዎችን ያስቀመጠው አዋጁ፣ የፕላስቲክ ምርቱ የአገልግሎት ዘመኑ ሲያበቃ እንዲሰበሰብ፣ ለዳግም ጥቅም ወይንም መልሶ ዑደት ላይ ሊውል የሚችልበትን ሥርዓት መፍጠር የፕላስቲክ ምርቱ የአገልግሎቱ ዘመን እንዳበቃ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ወጪ የመሸፈን ግዴታን በአምራቹ ላይ ጥሏል፡፡ የደረቅ ቆሻሻን ስለመሰብሰብ በተመለከተም ከሚመለከተው አካል በሚሰጥ ፈቃድ ለጥሬ ምርትነት ካልሆነ በስተቀር ደረቅ ቆሻሻን ወደ አገር ውስጥ ማስገባትንም ከልክሏል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የንፅህና መጠበቂያ እና የመዋቢያ ምርቶችን በጠርሙስ፣ በጣሳ ወይም በፕላስቲክ መያዣ የሚያመርቱ፣ የሚያስመጡ፣ የሚያከፋፍሉ ሰዎች ጠርሙሱ ወይንም የቆርቆሮ ጣሳው የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ መልሶ የሚወገድበትን ዘዴ የመዘርጋት ግዴታ እንዳለባቸው ደንግጓል።

ይኽ የተሻሻለው አዋጅ በእንደራሴዎቹ ከመጽደቁ ከጥቂት ወራት በፊት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድም በጉዳዩ ላይ መናገራቸው ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነባ ያለውን ኹለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት ሥራን በገመገሙበት ወቅት፣ ፕላስቲክን በተመለከተ መንግሥታቸው ሕግ እያዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው ነበር።

ይኽ የተሻሻለው አዋጅ በእንደራሴዎቹ ከመጽደቁ ከጥቂት ወራት በፊት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድም በጉዳዩ ላይ መናገራቸው ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በአዲስ አበባ ከተማ እየተገነባ ያለውን ኹለተኛው ዙር የኮሪደር ልማት ሥራን በገመገሙበት ወቅት፣ ፕላስቲክን በተመለከተ መንግሥታቸው ሕግ እያዘጋጀ መሆኑን ጠቁመው ነበር። ፕላስቲኮች ወደ አገር ውስጥ የማይገቡበትን መንገድ ለመፍጠር እንሞክራለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በሚታይ ኹኔታ መንገዶች ላይ የሚሠሩ የፕላስቲክ ቤቶች እና የፕላስቲክ በረንዳዎች መከልከል እንዳለባቸው መናገራቸው ይታወሳል። ማንም ሰው በቤቱ በረንዳ ላይም ይሁን ቡና ለመሸጥ በፕላስቲክ የሚሠራ ቤት ሕገ ወጥ መሆን አለበት ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ መጀመሪያ ላስቲክ ነው፣ ቀጥሎ ነው ሕጋዊ ቤት የሚመስለው፤ እናም፣ ፕላስቲክ የሚባል መፈቀድ የለበትም ሲሉ ጠንከር አድርገው ተናግረው ነበር።

## የአዋጁ ፋይዳ

በግንቦት ወር የጸደቀውን የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ አስመልክቶ፣ የፕላስቲክ ከረጢቶችን ማገድ አስመልክቶ ኢትዮጵያን የተለየ የሚያደርጋት አይደለም። ለምሳሌ ያህል ከኬንያ እስከ ሞሮኮ ያሉ የአፍሪካ አገራት ቀደም ብለው የፕላስቲክ ከረጢቶችን ሕዝባቸው እንዳይጠቀም ከልክለዋል። ከዚህ አኳያም፣ በጠቀስነው አዋጅ ውስጥ የተካተቱት የፕላስቲክ ከረጢቶች ዓይነቶች ላይ ካልሆነ በቀር፣ መልሶ ጥቅም ላይ የማይውሉ የፕላስቲክ ዓይነቶችን በመክልከል

ሥነ-ምኅዳሩን ከመበለሻሸት ለመጠበቅ መሞከር ቀዳሚው በጎ የአዋጁ ጎን ነው ብለን እናምናለን። የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ የፕላስቲክ ምርቶች ከአካባቢ ጽዳት አንፃር በጣም አስቸጋሪ ናቸው። የችግርነቱ መነሾም፣ አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል የሚጠቀምባቸው እነዚኽ ምርቶች በቀላሉ መገኘታቸው እና ከተጠቀምንባቸው በኋላም በአግባቡ አለመወገዳቸው ነው። የዚኽ አዋጅ መሠረታዊ ጠንካራ ጎንም፣ እነዚኽ የፕላስቲክ ከረጢት ዓይነቶች ዳግም በሌላ የምርት ሂደት ውስጥ በማለፍ ጥቅም መስጠት እስካልቻሉ ድረስ፣ መከልከላቸው ሥነ-ምኅዳሩን ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለውም በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ነገሩን ከነባሩ ኹኔታ አኳያ ልንመለከተው ብንሞክርም፣ የምንደርስበት መደምደሚያ ከዚኽ አይርቅም። ለዚኽም ማሳያ የሚሆነው፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት ላለፉት ጥቂት ዓመታት እየተተገበረ ያለው የአረንጓዴ ልማት ነው። እንደሚታወቀው፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የተለያዩ ኢንሼቲቮች እንደ አገር ተግባራዊ እየተደረጉ ናቸው። ከእነዚኽም መካከል የወንዝ ዳርቻ ልማት፣ የኮሪደር ልማት፣ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር የሚሉት ይገኙበታል። ከዚኽ አንፃርም፣ አገራችን ከያዘችው አረንጓዴ ኢኮኖሚ መርኃ ግብር አንጻር የአዋጁ መሻሻል ይበል የሚያስብል ነው።

ጠቅለል አድርገን ከላይ ካየነው የአዋጁ አገራዊ ፋይዳ ባለፈ፣ ምንም እንኳን ዝቅ ብለን በአጭሩ የምናያቸው ውስንነቶች መኖራቸውን አሌ ባይባልም፣ አዋጁ የሚመለከታቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ዝቅተኛው የኢኮኖሚ ዕርከን ላይ ያሉትን ጭምር እንደመሆኑ፣ ለተፈፃሚነቱ የሽግግር ጊዜ መስጠቱ የአዋጁ አንድ መልካም ጎን ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። የአዋጁ ተፈጻሚነት ከመውጣቱ በፊት የተመረቱ እና ወደአገር ውስጥ የገቡትን እንደማይመለከት ሲገለጽ፣ ለዚኽም የስድስት ወራት ጊዜ እንደሚሰጥ በበላሥልጣናቱ ጭምር መነገሩን በበጎነት መውስድ ይቻላል። ከዚኽ በተጨማሪም፣ አዲሱ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በኋላ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት የሽግግር ጊዜ መሆናቸው፣ በተለይም የተከለከሉት ምርቶች በሰፊው ሕዝብ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከመሆናቸው አንፃር ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ለማዘጋጀት መታቀዱን በአዎንታዊ እርምጃነት ብሪጅ ይመለከተዋል። በእነዚኽ ስድስት የአዋጁ የሽግግር ወራትም፣ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን ብቻም ሳይሆን፣ አዋጁን መተግበር የሚያስችሉ ወጥ አገር ዓቀፍ አሰራሮችን መዘርጋት እና ማቀናጀት ላይ የሚሰራበት ወቅት እንዲገኝ ያስችላልና፣ በእነዚኽ ወራት የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ይሰራሉ ብለንም ተስፋ እናደርጋለን። ከዚኽ አኳያም፣ ለአንድ ጊዜ የሚያገለግሉ የፌስታል ምርቶች መከልከላቸውን ተከትሎ ቀድሞ በዚኽ ዘርፍ የነበሩ አምራቾች በሌላ ተኪ ምርት ላይ እንዲሰማሩ የሚያስችሉ የትብብር ማዕቀፎች ተዘጋጅተው እንደሚተገበሩ መነገሩን በበጎነት እንወስዳለን።

ብሪጅ፣ ከነጣላ ድንጋጌዎች አንፃርም፣ ማሳያ ይሆኑ ዘንድ ኹለት የአዲሱን አዋጅ ድንጋጌዎች ማንሳት ይፈልጋል። በቀዳሚነት፣ ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቤቱ ድንበር አንስቶ ከሃያ ሜትር በላይ አካባቢውን የማጽዳት ግዴታ በአዋጁ መቀመጡን ማንሳት ይቻላል። ይኽ ድንጋጌ፣ ዜጎች ለራሳቸውም ሆነ ለማኅበረሰባቸው የተሻለ ኃላፊነት እንዲወስዱ አበረታችነት አለውና፣ ይኽ የአዋጁ ጥሩ ድንጋጌ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ከዚኹ የዜጎች ኃላፊነት ጋር በተያያዘም፣ ማንኛውም የአገልግሎት መስጫ ወይም የንግድ ተቋም በየፈርጁ የተለዩ ምልክት የተደረገባቸው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች አመቺ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ እንዳለበት መደንገጉንም እንዲኹ በነጠላ የአዋጁ አበርክቶነት ሳንቆጠር አናልፍም።

## የአዋጁ የትግበራ ውስንነቶች

ለዐሥራ ስምንት ዓመታት በሥራ ላይ የነበረውን ይኽን አዋጅ መሻሻል አስመልክቶ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተችቶ ሲነሱ ተስተውሏል። አንዳንዶቹን ትችቶችም ብሪጅ ይጋራቸዋል። ለማሳየነትም፣ የዚኽን አዋጅ ከስድስት ወራት በኋላ ወደ ሥራ መግባት ተከትሎ፣ በተወሰኑ የኢንዱስትሪው ክፍሎች ላይ ሊያጋጥም የሚችለውን የሥራ ዕድል ማጣት ማንሳት ይቻላል። እንደሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ አንድ ሺሕ የሚጠጉ የፕላስቲክ እና ጎማ አምራች ፋብሪካዎች ይገኛሉ። በቀላሉ መገመት እንደሚቻለውም፣ እነዚኽ ፋብሪካዎች በሥራቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞችን ቀጥረው ያሰራሉ። ከፋብሪካዎቹ ተፈጥሮ እና ከምርቱ አንጻር ብዙዎቹ እነዚኽ ሠራተኞች አንስተኛ የትምህርት ዝግጅት እና የሙያ ደረጃ ያላቸው ናቸው። እናም፣ ምንም እንኳን አዋጁ አንድ መንፈቅን የሽግግር ጊዜ እንደሆነ ቢያትትም፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ካለበት ነባራዊ ኹኔታ አንፃር፣ እነዚኽ ፋብሪካዎች ወደ ሌላ ክፍለ-ኢኮኖሚ ለመሻገር ስድስት ወራት ይበቃቸዋል? የሚለው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በተለየ ኹኔታም፣ መዘጋት አልያም ወደሌላ ክፍለ-ኢኮኖሚ መሻገር ብቸኛ ዕጣቸው በሆኑት እነዚኽ ፋብሪካዎች እና በስርጭቱ ሰንሰለት ውስጥ የሚገኙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት ሠራተኞች ዕጣ ፈንታም የከፋ እንዳይሆን አዋጁም ሆነ አዋጁን በተለያዩ



ምክር ቤቱ አዋጅ ቁጥር 513/1999ን በማሻሻል ላይ

የአስረጂ መድረኮች ያብራሩት የመንግሥት ባለሥልጣናት እና የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በበቂ ኹኔታ ሳያብራሩ ቀርተዋል። ይኽ ጉድለትም፣ በእነዚኽ የፋብሪካ ባለሀብቶችም ሆነ በሥራቸው ባሉት ሠራተኞች ዘንድ እጅጉን የተዘበራረቀ ኹኔታ መፈጠሩን ብሪጅ ተገንዝቧል። ይኽም ምናልባትም፣ የአዋጁ አተገባበር መሠረታዊ ዕግዳት አድርጎ በመቁጠር፣ ችግሩ ሳይከሰት ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት አንስቶ የሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት እና ራሱ የእንደራሴዎቹ የተጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴ አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያበጅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ ጎን ይኽንኑ ጉዳይ ስንመለከተው ደግሞ የምናገኘው ሌላኛው የአዋጁ የአተገባበር አሉታዊ ተጽዕኖ፣ መንግሥት ለእነዚኽ ፋብሪካዎች በዓመቱ ያገኝ የነበረውን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያለሆነ የግብር ገቢ በምን መልኩ ሊተካ እንዳሰበ ሲነገር አለመደመጡ ነው። ይኽም፣ በቀጥታ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር የተያያዘ ጉዲለት ባይሆንም ቅሉ፣ ተራዛሚ የአዋጁ አሉታዊ ተጽዕኖ ነውና፣ ልብ ይባል የሚል ምክረ-ሐሳባችንን ማቅረብ እንሻለን።

ከተሻሻለው አዲሱ አዋጅ ነጣል ድንጋጌዎች አኳያም፣ አንድ ጉድለትን አለማንሳት አይቻልም። ይኸውም፣ ማንኛውም ሰው ፕላስቲክ ይዞ ከተገኘ ከኹለት እስከ አምስት ሺህ ብር እንደሚቀጣ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ ነው። በዚኽ ድንጋጌ ዙሪያ የምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ ሲናገሩ፣ ለአንድ ጊዜ ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ፌስታሎችን ዝቅተኛው የማኅበረሰብ ክፍልም ስለሚጠቀማቸው ቅጣቱ ያን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው ማለታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። ነገሩን በምሳሌ ሲያስረዱም፣ "ለምሳሌ አንዲት አሮጊት ወይም ሽማግሌ የሁለት ብር ዳቦ ወይም የአስር ብር ስኳር ገዝተው ሲሄዱ 5 ሺህ ብር ክፍሉ ቢባሉ ላይኖራቸው ስለሚችል፣ ቅጣቱ ከ5 ሺህ ወደ 2 ሺህ ዝቅ እንዲል ተደርጓል ብለዋል ተብሏል። ይኽ የቅጣት ዕርከን፣ ሰብሳቢው እንዳሉት የ2 ብር ዳቦ ለገዙ አዛውንት እጅጉን የበዛ ይመስላል። በሌላ ጎኑ ስንመለከተው ደግሞ፣ በመንገዳቸው ላይ ሲጓዙ ይኽ ቅጣት ያገኛቸው አንድ አዛውንት፣ የተጠቀሰውን የቅጣት መጠን መክፈል ባይችሉ ሌላ እንደ ማኅበራዊ ግልጋሎት መስጠት የመሳሰሉ ቀላል ማኅበራዊ ቅጣቶች በአማራጭነት አለመቀመጣቸው ቢያንስ የአዋጁ አተገባበር ላይ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻም፣ ይኸው አዲስ አዋጅ በአገር ዓቀፍ ደረጃ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት የተጀመረውን የችግኝ ተከላ አገራዊ ንቅናቄ እንዳይጎትተው ስጋት አለ። እንደሚታወቀው፣ ለዚኹ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አገራዊ ዕቅድ በዓመቱ ከዐሥር እስከ ዐሥራ አምስት ቢሊዮን ችግኞች የሚተከሉባቸው የፕላስቲክ ከረጢቶች ያስፈልጋሉ። ምንም እንኳን መሰል ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በልዩ ሁኔታ በሚያወጣው መመሪያ ሊፈቅድ የሚችላቸው ነገሮች እንዳሉ በአዋጁ ቢጠቀስም፣ በዚኽ ጉዳይ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ አልያም፣ በቀጣዮቹ ስድስት የሽግግር ወራት ውስጥ፣ የተጠቀሱትን የአዋጁን አተገባበር ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተገዳሮቶችን ጭምር ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መመሪያ ቢወጣ ጠቀሜታው ብዙ ነው የሚለው የመጨረሻው የብሪጅ ምክረ-ሀሳብ ነው።

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.